የ ድ ሬ ዳ ዋ  አ ስ ተ ዳ ደ ር

# ድ ሬ  ነ ጋ ሪ ት  ጋ ዜ ጣ

# D I R E  N E G A R I T  G A Z E T A

## OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION

4ኛ ዓመት ቁጥር 21
ትሬቴ□ ጥቅምት 30 ቀን 2004

በድሬዳዋ አስተዳደር
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No.21
DIRE DAWA feb 8ht, 2011

## አዋጅ ቁ□ር 21/2004

### የድሬዳዋ አስተዳደር የአስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ  አዋጅ

የድሬዳዋ አስተዳደር የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 16/2003 ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የድሬዋ አስተዳደር ምክር ቤት በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ‹‹ሀ›› በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቶአል፡፡

## PROCLAMATION No 21/2011

### A PROCLAMATION TO AMEND THE PROCLAMATION ENACTED TO DEFINI THE POWERS AND DUTIES AND RE-ESTABLISHMENT OF THE EXECUTIVE AND MUNICIPAL SERVICE ORGANS OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION.

WHEREAS, it has been found necessary to amend the proclamation enacted for defining the powers and duties and for re-establishing the executive and

municipal service organs of the Dire Dawa Adminstration Proclamation No. 16/2010;

NOW, THERFORE, in accordance with Article 12 (1) (A) of the Dire Dawa Administration Charter Proclamation No. 416/2004, the Council of the Dire Dawa Administration, hereby proclaims the following amendment:

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ‹‹የድሬዳዋ አስተዳደር የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 21/2004›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ማሻሻያ

የድሬዳዋ አስተዳደር የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 16/2003 ዓ/ም እንደሚከተለው ተሻሽሎአል፡፡

1. በአዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (9) ስር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (10) እና (11) ተጨምረዋል፣

   ‹‹10›› የመሬት ልማት እና ማናጅመንት ቢሮ፣

   ‹‹11›› የኮንስትራክሽን እና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ቢሮ
2. የአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (10) ተሰርዞአል፡፡
3. የአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) ተሰርዞ ፊደል ተራ (ሐ) እና (መ) እንደቅደም ተከተላቸው ፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) ሆነዋል፡፡
4. የአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (2) ተሰርዞ ንዑስ አንቀጽ (3)፣ (4)፣ (5) እና (6) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (2)፣ (3)፣(4) እና (5) ሆነዋል፡፡
5. የአዋጁ አንቀጽ 12 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 12 ተተክቶአል፣

   ‹‹12›› <u>የስፖርት ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር</u>

   ኮሚሽኑ በድሬዳዋ አስተዳደር የስፖርት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 22/2004 ላይ የተገለፀው ሥልጣንና ተግባር ኖሩታል፡፡

## 1. Short Title

This proclamation may be cited as the " Amended Definition of the Powers and Duties and Re-establishment of the Executive and Municipal Service Organs of the Dire Dawa Administration Proclamation No,21/2011"

## 2. Amendment

The Definition of the Powers and Duties of the Executive and Municipal Service Organs of the Dire Dawa Administration Proclamation No,16/2010 is hereby amended as follows.

1. The following new Sub-Article (10) and (11) are added under Sub-Article (9) of Article 4 of the Proclamation.

   "10". Land Development and Management Bureau

   "11". Construction and Municipal Service Bureau

11. Make that urban development work implemented is integrated with poverty reduction effort; device a strategy for the expansion of micro and small scale enterprises; and execute the same, provide appropriate support for its implementation;
12. Device and put into effect a strategy for integrating the work of infrastructure expansion and construction development in the administration properly;
13. With out prejudice to the powers legally granted to other organs, lead and support the efforts to set up standards for construction work;
14. Follow up, control and ensure that municipal service organs are providing satisfactory service;

15. ከተማ ዓቀፍ □ና ቀበሌ ዘለል የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን በተመለከተ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ተቋማት □ቅድና በጀት እንዲዘጋጅ በማድረግ ለካቢኔው □ቀርባል፣ ሲናትቅም ተፅባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣
16. የአገልግሎት አቅርቦት መለኪያዎች □ና መመሪያዎች ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ በማድረግ ለካቢኔው □ቀርባል፣ሲ□ሰንም ተፅባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣ቀልጣፋ፣ውጤ□ማና ፍትሃዊ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት መሰጠቱንም □ረፋፅ□ል፣
17. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚመለከት □□ሊሲ ሃሳብ □ና የህግ ረቂቅ በማመንጨት ለካቢኔው □ቀርባል፣ ሲናትቅም ተፅባራዊ □□ርፋል፣
18. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚመለከቱ ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣
19. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን በተመለከተ የነዋሪዎችን አቤቱ□ ያስተናግዳል፣ለሚቀርቡ ጥያቄዎችም በተቻለ ፍጥነት ምላሽ ይሰጣል፣
20. የአቤቱ□ መንስኤዎች ወይም ምንጮች ተለይተው ጥናት እንዲደረግባቸው በማድረግ ዘላቂ መፍትሄ የሚሰጥበትን ሁኔ□ ያመቻቻል፣
21. በስሩ ከተደራጁ የስራ ክፍሎች □ና ተቋማት የተውጣጣ የስራ አመራር ኮሚቴ □ቋቁማል፣ጁመራል፣
22. አግባብ ካላቸው አካላት እና ከከተማው ነዋሪዎች ጋር በመተባበር በአጋርነት ይሰራል፣
23. ሌሎች አላማውን ለመፈፀም የሚረዱ ተመሳሳይ ተግባራትን ያከናውናል::

15. Have all the city–level municipal service rendering institutions with the exeption of Kebeles prepare their plan and budget; submit the same for the cabinet; and execute upon approval;
16. Cause the preparation of service delivery standards and directives and submit the same to the cabinet; execute it upon approval; ensure the delivery of effective, efficient, and fair municipal service;
17. Generate policy ideas and draft laws concerning municipal service and submit it to the cabinet, and execute the same upon approval;
18. Enforce decisions passed about municipal service;

19. Entertain complaints raised by residents regarding municipal service; and give response to the complaints without much delay;
20. By having the specific causes and sources of the complaints studied, prepare the condition for resolving the problems conclusively;
21. Establish and lead a management committee from the different departments in the bureau and other institutions affiliated to it;
22. Carry out its function by working in collaboration with with concerned organs and residents of the city;
23. Carry out other activities deemed necessary for the realization of its objectives;

6. የአዋጁ ክፍል አራት ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ክፍል አራት ተተክቶአል፤

**ክፍል አራት**

**ስለኮንስትራክሽን እና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት**

7. የአዋጁ አንቀጽ 37 እና 38 ተሰርዘዋል፣
8. የአዋጁ የቀድሞ አንቀጽ 33, 34, 35, 36, 39, 40,41,42 እና 43, እንደቅደም ተከተላቸው 34,35,36,37,38,39,40,41, እና 42 ሆነዋል፣
9. የአዋጁ አንቀጽ 34 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 34 ተተክቶአል፤

‹‹34›› **የኮንስትራንሽን እና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት መቋቋም፤**

1. የሚከተሉት የኮንስትራክሽን እና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት ህጋዊ ሰውነት በማግኘት ተቋቁመዋል፣
   ሀ. የጽዳት፣ ውበትና የመናፈሻ ልማት ኤጀንሲ፤
   ለ. የቁራ አገልግሎት ድርጅት፣
   ሐ. የጥቃቅን እና አነስተኛ ንግድ ልማት ኤጀንሲ፣
   መ. የቤቶች ልማት ማናጅመንት እና ኮንስ ትራክሽን ኤጀንሲ፣
   ሠ. የደንብ ማስከበር እና የነዋሪዎች አገል ግሎት ጽህፈት ቤት፣

2. እያንዳንዱ የኮንስትራክሽን እና የማዘጋጃ ቤታዊ አልግሎት አካል የራሱ የሆነ የሥራ ክፍሎች እና ሠራተኞች ይኖሩታል፣

6. Part Four of the amended Proclamation is repealed and replaced by the following new PART FOUR

**PART FOUR**

**ORGANS OF CONSTRUCTION AND MUNICIPAL SERVICE**

7. Article 37 and 38 of the Proclamation are revoked
8. In the amended Proclamation Articles 33,34,35,36,39,40,41,42 and 43 of the Proclamation are re-numbered as Articles 34,35,36,37,38,39,40,41 and 42 respectively.

9. Article 34 of the Proclamation is repealed and is replaced by the following new Article 34.

**"34". <u>Establishment of Organs of construction and Muncipal service</u>**

1. The Construction and Municipal Aervice Organs of the administration that have legal personality are the following:

   a. Sanitation, Beautification and Pparks Development Agency;
   b. Abattoir Service;
   c. Mico and Small Scale Business Development Agency;

   d. Housing development, Management and Construction Agency;
   e. Code Enforcement and Resident's Service Office;

2. Each of these units in the Construction and Municipal Service Organ shall have its own working sections and employees;

3. የኮንስትራክን እና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት እንዳስፈላጊነቱና አመቺነቱ እንደ ህግ አገልግሎት እና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶችን በጋራ ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ የአስተዳደሩ ካቢኔ በሚያፀድቀው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት ይወሰናል፡፡

10. የአዋጁ አንቀጽ 35 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 35 ተተክቶአል፤

‹‹35››በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ(1)የተጠቀሱት የኮንስትራክሽን እና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት ተጠሪነታቸው ለኮንስትራክሽን እና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ቢሮ ይሆናል፡፡

11. የአዋጁ አንቀጽ 36 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 36 ተተክቶአል፤

‹‹36›› <u>ስለሌሎች የኮንስትራክሽን እና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት</u>፤

1. የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፤
2. የመንገዶች ባለስልጣን፤ እና
3. የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት፤ ተጠሪነት ለኮንስትራክሽን እና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ቢሮ ሆኖ ቀደም ብለው በተቋቋሙባቸው ህግ በተደነገገው መሠረት ስራቸውን ይቀጥላሉ፤

12. ከአዋጁ አንቀጽ 42 ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጽ 43, 44, እና 45 ተጨምረዋል፡፡

3. The organs of Construction and Municipal Service can commonly use the services of the the supporting staff such as the legal service section whenever they find it necessary and convienient. The particulars of the organizational structures, in this regard, shall be approved by the cabinet of administration.

10. Article 35 of the amended Proclamation is repealed and is replaced by the following new Article 35:

"35" The Construction and Municipal Service Organs specified in Article 35, Sub–Article (1) shall be accountable to the Construction and Municipal Service Bureau;

11. Article 36 of the Proclamation is repealed and is replaced by the following new Article 36.

**"36" <u>Regarding other Construction and Municipal Service Organs</u>.**

1. Water and Sewerage Authority;
2. Roods Authority; and
3. Housing Development Project Office

These organs are also accountable to the Construction and Municipal Service Bureau. And

they shall continue their function in accordance with the legal proclamation used for their establishment;

12. The following three new articles – Articles 43,44,and 45 are added in the amended Proclamation:

‹‹43›› <u>**የጥቃቅን እና አነስተኛ ንግድ ልማት ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር**</u>

**ኤጀንሲው፡-**

1. **የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፤**
2. **ዘርፉን በሚመለከት የፖሊሲ ጥናቶችን፣ የም ርምር ስራዎችንና ስትራቴጂክ ፕላኖችን እያጠና ያቀርባል፡፡ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤**
3. **በፌዴራል ደረጃ የአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋማትን ለማስፋትና ለልማት የወጡትን ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን መሰረት በማድረግ በከተማው አስተዳደር ውስጥ ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ተቋማት እንዲስፋፉና እንዲለሙ በማድረግ ለኢንዱስትሪ ልማት መሰረት እንዲሆኑ ያደርጋል**
4. **ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ለማስፋፋትና ድጋፎችን ለመስጠት የሚያስችሉ መመሪያዎችን፣ ደንቦችንና ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፡፡ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤**
5. **የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ከማስፋትና ድጋፎች ከመስጠት አኳያ ከመንግስታዊ እና ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንዲሁም ከተለያዩ ማህበራት ጋር ግንኙነት በመፍጠር የሚደራጁ ኢንተርፕራይዞችን የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤**
6. **ሴክተሩን ለማስፋትና ለማልማት ጠቃሚ የሆኑ የፖሊሲ ሀሳብ ለማመንጨት የሚ ረዱ የተለያዩ ጥናቶች እንዲከናወኑ ያደር ጋል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከ ታተላል፤**

"43" <u>**Powers and Duties of Micro and small scale Business Development Agency**</u>

**The Agency shall:-**

1. Organize, administer, and coordinate micro and small scale enterprises;
2. Undertake policy studies, research work and strategic plans pertaining to the sector, submit the result to the concerned; up on approval implement the same;
3. By expanding and developing micro and small scale enterprises in accordance with the policies and strategies formulated at Federal level, endeavour to make micro and small scale enterprises foundations industial development;
4. Prepare regulations, directives, and standards that support the expansion of the micro and small scale enterprises; submit the same to the concerned body; and up on approval, follow–up the implementation of the same;
5. In order to help the expansion of the micro and small scale business enterprises, create conditions for newly organized micro and small scale

business enterprises to get material and financial support by establishing relations with governmental, Non–governmental organizations, and different associations;

6. In order to expand and develop the sector, cause the undertaking of various studies intended to generate useful policy concepts; submit the same to the concerned body; upon approval, follow up the implementation;

**7.** የቢዝነስ ኢንኩቬተሮችንና ማሰልጠኛ ማዕከላትን እንዲቋቋሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

**8.** በከተማው ውስጥ የሚገኙትን ስራ አጥ የሆኑ ወጣቶችና ሴቶችን በብዛት በማሳተፍ አምራች ዜጋ ሊያደርጉ የሚችሉ የተለያዩ ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ተቋማት ፕሮጀክቶች እንዲጠኑ ያደርጋል፣ ተግባራዊነታቸውንና ውጤት ማስገኘታ ቸውን ያረጋግጣል፤

**9.** የዘርፉ ምርቶች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ገበያ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ ምርቱን ለማስተዋወቅና ህብረተሰቡን ስለ ተቋማቱ ጠቀሜታ ግንዛቤ እንዲኖረው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ ስለቶችን ይቀይሳል፤ ትምህርታዊ መግለጫዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤

**10.** ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት የሚውል መረጃ ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤ የድጋፎች ፍላጎትና አቅርቦት ጥናት ያካሂዳል፤

**11.** የጥቃቅንና የአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ቡድንን የማደራጀት፣ የስልጠና እና የብድር አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂና የማምረቻ መሳሪያዎች አቅርቦት ያመቻቻል፣ የገበያ ትስስር ድጋፍ ይሰጣል፤

**12.** ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የማምረቻ፣ የመሸጫ ቦታና ቤት ያቀርባል፤ የኤክስቴንሺን እና የንግድ ልማት አገልግሎት ያመቻቻል፤

**13.** ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ለማልማትና ለማስፋት የፕሮሞሽንና የሕዝብ ንቅናቄ ስራዎች ያከናውናል፤

7. Create condition for the establishment of business incubators and training centers;

8. By having different micro and small scale business enterprise projects studied, endeavour to create wider working opportunity for the unemployed youth and women and make them productive citizens; submit the same to the concerned body; ensure their implementation and their effectiveness;

9. Facilitate conditions that provide for product of the sector marketing access at national and international level; in collaboration with other concerned organs devises strategies for promoting the products and creating awareness about the importance of the institutions among the community, have educational explanation prepared; coordinate the implemntation and follow–up;

10. Gather, and compile data that can be used for the development of micro and small scale business enterprises; and distributes the same to users; undertake need assessment study;

11. Facilitate organizing of micro and small scale business enterprise teams, training and credit service; supply of technology and production equipment; and provide support for creating marketing linkages;

12. Provide manufacturing sheds, and marketing stalls; facilitate extension; and business development services for micro and smallscale business enterprises;

13. Carry out promotion and community mobilization work to develop and expand micro and small scall business enterprises;

**14. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የኦዲትና የኢንስፔክሽን አገልግሎት ይሰጣል፤**

**15. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግ ባራትን ያከናውናል::**

**‹‹44›› <u>የቤቶች ልማት ማናጅመንት እና ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር</u>**

**ኤጀንሲው፡-**

1. ዘርፉ የሚመራበትንና እንዲሁም ቤቶችን የሚመለከቱ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች አ□ፉፀቶ □ቀርባል፣ ሲፀድቁም ተፈፃሚነታቸውን ያረጋግጣል፣

2. አስፈላጊ ሲሆን በአስተዳደሩ በጀት ለሚገነቡ ግንባታዎች የሚያገለግሉ ውሎችና ውሎች ስለሚይዟቸው የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች ዝርዝር የቴክኒክ መመርያ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጋር በመመካከር በማዘጋጀት በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

3. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዕድገት ከግብዓት አቅርቦት ጋር መጣጣም እንዲችል የግንባታ ግብዓት አምራቾችና አከፋፋዮች በጥራትና በብዛት እንዲያቀርቡ ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፣ ይደግፋል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣

4. የኮንስትራክሽን ዘርፍ የመረጃ መረብና ማዕከል እንዲኖር በማድረግ ወቅታዊ የዘርፉ መረጃዎች ተሰብስበው፣ ተመዝግበውና መረጃዎች ተተንትነው የልማት አቅጣጫዎችን መጠቆም በሚችሉ አግባብ መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፣

14. Provide auditing and inspection service for the micro and small scale business enterprises;

15. Undertake other activities necessary for the fulfillment of its objectives.

**"44" <u>Powers and Duties of Housing Development, Management and construction Agency</u>**

The Agency shall :-

1. Prepare and submit proclamations, regulations and directives for guiding the work of the sector itself for issues pertaining to housing; and ensure their enforcement upon approval;

2. Whenever necessary, prepare and put into effect agreement documents for government financed constructions in consultation with

the Finance and Economic Development Bureau about the detailed technical directives, terms and conditions of the contract.

3. Device strategies for making the quality and quantity of construction inputs supplied by producers and distributors is compatable with the growth of the costruction industry; support and follow up the same;

4. By setting up a website and database center for the construction sector, ensure the timely collection, registration, and interpritation of the data concerning the sector, and the organizing of the outcome in such a way as to indicate future development directions.

5. በመንግስትና በሌሎች አካላት ለሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች የመሠረተ ልማት አቅርቦት እንዲሟላ የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል፣

6. ለቤት ልማት የሚያስፈልግ የመሬት፣ የመሠረተ ልማት አቅርቦት በዘላቂነት የሚረጋገጥበትንና እንዲሁም የፋይናንስ አማራጭ በማጥናት ለአፈፃፀም የሚረዳ የአሰራር ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፣ በአፈፃፀም ይደግፋል፣

7. ለቤቶች ልማት አጋዥ የሆኑ አማራጭ የግንባታ ግብአቶች እንዲቀርቡ ይደግፋል ያስተባብራል፤እንዳስፈላጊነቱ ወጭ ቆጣቢ የግንባታ እቃ የሚያመርቱ ፋብሪካዎችንና ተጓዳኝ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ያቋቁማል፣አፈፃፀማቸውን ይገመግማል፡፡

8. በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የተወረሱና አስተዳደሩ የገነባቸውንና የሚገነባቸውን ቤቶች ያስተዳድራል፤ በሕግ አግባብ ለተጠቃሚው አገልግሎት መዋላቸውንና አዲስ የሚገነቡ ቤቶችም በደንቡ መሠረት ለተጠቃሚዎች መተላለፋቸውን ያረጋግጣል፣

9. የመኖሪያ ቤት እጥረት ማቃለል እንዲቻል የተለያዩ አማራጮችን ያስጠናል፤ እንዲሁም በአካባቢ ማቴሪያሎች የሚገነቡ ስታንዳርድ ዲዛይኖችን በማዘጋጀት አነስተኛና መካከለኛ ገቢ ላላቸው የከተማው ነዋሪዎች ተገቢ የጥራት ደረጃቸውን የጠበቀ፣ ወጭ ቆጣቢና በዋጋ ተደራሽ ቤቶች በስፋት እንዲገነቡ ያስተባብራል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፣

5. Coordinate the efforts of concerned bodies for the provision of all the infrastructures for condominium homes built by government and other organs;

6. Create a working system that is supportive of implementation by sustainably ensuring the availability of land for housing development, and the supply of infrastructures as well as by studying financial alternatives; support the implementation of the same;

7. Support and coordinate the supply of alternative construction inputs that are supportive of housing development; and when becomes necessary establish cost effective construction material producing industries and institutions that provide other related services; and evaluate their performance;

8. Administer houses confisicated by Proclamation No. 47/67 and the houses already constructed and those yet to be constructed by the administration; and ensure that they are providing service for their users in accordance with the law and that the newly constructd are handed over to their users according to regulation;
9. Have different alternative studies undertaken to reduce the shortage of residential houses; coordinate increased construction of standardized, cost effective, and low cost houses for low and medium income earning residents of the city by preparing standard designs for houses to be constructed using locally found materials; and follow up the execution of the same;

10. በአስተዳደሩ በጀት ለሚሰሩ የመኖሪያ ቤቶችና የመንግሥት ህንፃዎች ዲዛይኖች፣ ፕላኖችና የስራ ዝርዝሮች በራስ ኃይል ወይንም በአማካሪ ድርጅት በጥራት እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤
11. በአስተዳደሩ የሚገነቡትን የመኖሪያ ቤቶችና ሌሎች የመንግሥት ሕንፃዎች በተገባለት ውል መሠረት የጥራት ደረጃቸው፣ የጊዜና የዋጋ ገደቦች ተጠብቀው መሠራታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
12. ህዝቡ የልማቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ እና ተሳታፊ እንዲሆን ለማድረግ በሚሰሩ ልዩ ልዩ የአካባቢ ልማት ሥራዎች ላይ ድጋፎችን ያደርጋል' የልማት ሥራዎችን አፈፃፀም ይገመግማል፤
13. ለጎርፍ የተጋለጡ የከተማዋን ክፍሎች በተመለከተ የመከላከል ሥራው ያለበትን ደረጃ ይገመግማል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡
14. የሴክተሩ መደበኛና ካፒታል በጀት ጠይቆ በማስፈቀድ ያስተዳድራል፣
15. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ከቢሮው የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፣

10. By using either its own manpower or a consultant firm, have good quality designs, plans and work details prepared for residential homes and public buildings to be built with budget allocated by the administration;
11. Put into effect a controlling system for ensuring that the construction of government financed residential homes and public buildings is carried out in accordance with the agreement signed with respect to quality of work, time, and cost limitations; follow up and supervise the same;
12. Provide support for different local development activities that are intended to make the public direct beneficiary and participant of development; and evaluate the performance of community development activities;

Constitution and Municipal Service Bureau while it shall be appointed by the cabinet;

14. Sub-Article (4) of Article 48 of the Proclamation is repealed and is replaced by the following two new sub-Articles (4) and (5);

**“48”** (4) The powers and duties assigned to the Cty Manager Office is hereby transferred to the Construction and Municipal Service Bureau;

“48” (5) The powers and duties assigned to the Land Development and Administration Authority is hereby transferred to Land Development and Management Burea.

**3. <u>Effective Date</u>**

This proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Dire Negarit Gazeta.

**Done at Dire Dawa, this** feb 8th **day of 2011**

**Assed Ziyad**

**Mayor of Dire Dawa Administration**